
በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



# የአስር ቀን የአየር ሁኔታና

# ትንበያ መጽሔት

## ከጁን 21-30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

## እና ግምገማ

## እንዲሁም 1-10፣ 11-20 ጁላይ 2024

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ  ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ....- 1 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 3 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ....- 3 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....- 3 -
እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 4 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 4 -
....- 4 -
እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....- 4 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....- 5 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 6 -
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 7 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ....- 7 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ....- 7 -
ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....- 8 -
....- 8 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 9 -
እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ....- 9 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በምስራቅ፣ በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጠንካራ እና የተስፋፋ የደመና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በብዙ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በባህርዳር 34.2 እና 32.5፤ በጎንደር 31.5፤ በጎሬ 45.3፤ በመተሃራ 52.3፤ በነቀምቴ 31.1፣ 44.3፤ በአቦምሳ 36.5፤ በአዴት 40.4፣ በአምቦ 37.8፤ አፅቢ 40.0፤ በአልጌ 55.0፤ በአንገርጉትን 32.0፤ በአሶሳ 54.0 እና 51.7፤ በአይከል 37.9 እና 37.8፤ በቻግኒ 35.0፤ በደብረወርቅ 30.4፤ በዳንግላ 33.7፤ በደባርቅ 87.2 እና 50.0፤ በኢጃጂ 31.2፤ በፍቼ 32.6 እና 38.1፤ በእምድብር 31.4፤ በካቺሴ 50.5፣ 33.0 እና 32.6፤ በላይበር 31.0፤ በሊሙ ገነት 87.7፤ በማጀቴ 31.8፤ በማሻ 40.6፤ በመተማ 32.2 እና 32.7፤ በሞጣ 30.0፤ በመካነ ሰላም 32.1፤ በሻምቡ 37.7 እና 32.1፤ በአዳማ 32.8፤ በወረኢሉ 33.7፤ በየትኖራ 30.4፤ በባቱ 31.6፤ በሂርና 32.6፤ በኮምቦልቻ (ምስራቅ ሀረርጌ) 38.8 እንዲሁም በጨለንቆ 30.4 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

ባለፉት ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ ዋህግምራ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ አዊ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፤ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ እንዲሁም ባሌ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ መተከል፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ ኑዌር፣ አኝዋክ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል ፋፋን እና ሲቲ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ሀላባ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ኮንታ፣ ከፋ፣ ሸካ እና ዳዉሮ ዞኖች፤ ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ ከ81-228 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ6-10 ቀናት ያህል ዝናብ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ነበራቸው። በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ባሌ እና ምዕራብ አርሲ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል አውሲ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጌዲኦ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ከንሶ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከ5-30 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ቄለም ወለጋ፣ ጅማ እና ኢሉባቦር ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ እና ፋፋን ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ማዕከላዊ፣ ሰሜን ምዕራብ እና ምዕራብ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ አዊ እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ካማሺ፣ አሶሳ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ፣ አኝዋክ፣ ኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አማሮ፣ ኣሪ፣ ባስኬቶ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌዲኦ፣ ኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ እና ወላይታ ዞኖች፣ ሁሉም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ሀረር እና ድሬዳዋ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት የነበረው እርጥበት ለመኸር የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን፣ አስቀድመው ለተዘሩም ሆነ በመዝራት ላይ ለነበሩ እንዲሁም በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀደም ብለው ለተዘሩ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው:: በተጨማሪም በምስራቃዊ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚገኙ የአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የተገኘዉ እርጥበት ለሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበቱም በላይ የተሻለ የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት እንዲኖር ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4)፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ አፋር ደናክሌ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቤ ሸበሌና ኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከ እርጥበታማ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት መጠን አግኝተዋል። ይህም ሁኔታ ለገጸ ምድርም



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሆነ ለከርሰ ምድር የውኃ ሀብት መሻሻል እንዲሁም የግድቦችን እና የወንዞች የውኃ አቅም ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው (ካርታ 5) ፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ የመጀመሪያው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛው እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡


በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ይበልጥ ይጠናከራሉ፡፡ ስለሆነም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን፣ በመካከለኛው እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6) ፡፡ በተጨማሪም በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ ቄለም ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፣ ዋህግምራ፣ አዊ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ ከትግራይ ክልል ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፤ ማዕከላዊ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ ፓዊ፤ አሶሳ፤ ካማሺ ዞኖች እና ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሃዲያ፣ ሀላባ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ የየም ዞኖች፣ ጠምባሮ፣ ቀቤና እና ማረቆ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዳውሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ኮንታ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌድኦ፣ ባስኬቶ፣ አማሮ፣ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በተጨማሪም ከዕለት ወደ ዕለት ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ ዞኖች፤




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሀረር እና ድሬ ዳዋ፣ ከጋምቤላ ክልል ንዌር፣ አኝዋክ፣ ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፣ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀረር፣ ኤረር፣ ኖጎብ፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ጋቢ እና ሀሪ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንሶ፣ አሪ ደራሼ፣ ቡረጂ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10, 2024 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሀለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ የሚጠናከሩ ሲሆን፣ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተስፋፋ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡


በመጪዉ የጁላይ ሁለተኛዉ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ፡፡ በመሆኑም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋና ጠንካራ የደመና ክምችት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አካቢዎች ላይ ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸል (ካርታ 8) ፡፡

Rainfall performance (mm) for 11-20 July 2024




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት የሚኖረው እርጥበት ወቅታቸውን ጠብቀው ለሚዘሩ የመኸር ሰብሎች ማለትም የጥራጥሬ ሰብሎችን፣ የቅባት እህሎችን፣ የጓሮ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን ለመዝራትና ማሳን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ከመጋቢት መጨረሻ ጀምሮ ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ለሚገኙ የረጅም ጊዜ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎትን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል የሚጠበቀው እርጥበት የክረምት ተጠቃሚ በሆኑት የምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ አካባቢ በሚገኙ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የአረንጓዴ እጽዋት ልምላሜን፣ የግጦሽ ሳርንና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል።

በአንፃሩም ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑና በረባዳማ አካባቢዎች ላይ የሰብሎች በጎርፍ የመጠረግ እና የአገፈር መሸርሸር ሊከሰት ስለሚችል ይህንን ለመከላከል የሚያስችል የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችንና የውሃ ማንጣፈፊያ ዘዴዎችን ከወዲሁ በማዘጋጀት አስፈላጊውን የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች ማከናወን ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉ.ሀዉ. ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም በአፋር ደናክል በታችኛው አዋሽ እንዲሁም በመካከለኛው ገናሌ ዳዋ መካከለኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ይህም ሁኔታ የግድቦች የውሃ መጠንን ከማሻሻል እንዲሁም የወንዞችን እና ሌሎች ውሃማ አካላት የተሻለ የውኃ መጠን እንዲኖራቸው ከማስቻል አንጻር አዎንታዊ ሚና እንደሚኖረው ይጠበቃል፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et